የሰ/መ/ቁ.102144

ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** ቫዮሌት አጠቃላይ ንግድ ሥራ ኃላፊነቱ የተወሳነ የግል ማህበር አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** ሐግቤስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ነገረ ፈጅ ፀጋዬ መካሽ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን የሚከተለዉን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20426 ሀምሌ 22 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 142/66 ሰኔ 2 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠራታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንድታረምልኝ በማለት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዩ በቼክ የተከፈለ የመኪና ዋጋ የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች በአምስት ቼኮች ፅፎ የሰጠውንና በከፊል በዱቤ ገዝቶ የተረከባቸው መኪኖች ዋጋ ሃምሳ ፐርሰንት ጠቅላላ ድምሩ 435,554.44/ አራት መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ አራት ብር ከአርባ አራት ሣንቲም/ ወጭ አድርጎ ከሰጡት በኃላ ቼኮቹን ለክፍያ ከመቅረቤ በፊት እንዳይከፈል በመጋዱ ገንዘቡ ሣይከፈለኝ ቀርቷል፡፡ ስለዚህ ገንዘቡን ከዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር እንዲ ከፍል የወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡አመልካች ተከሳሽ ሆኖ ቀርቦ የሸጠልኝ መኪኖች የምርት ጥረት ጉደለት ያለባቸው በመሆኑና ከሳሽም ጉድለቱን ለማስተካከል ፈቀደኛ ባለመሆኑ ቀሪውን የመኪኖቹን ዋጋ ለመክፈል አልገደድም በማለት ተከረክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች ይግባኝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሰኔ 14 ቀን 2006ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የሸጠልኝ መኪናዎች የምርት ጥራት ጉድለት ያለባቸው ናቸው፡፡ተጠሪ ጉድለቱን እንዲያስተካክል ሲጠየቅ ፈቀደኛ አልሆነም፡፡አመልካች ቀሪውን የመኪኖቹን ዋጋ

የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ተጠሪ የበኩሉን ግዴታ በአግባቡ ሲወጣ በመሆኑ በቼክ የታዘዘው ገንዘብ እንዳይከፈል ማገዱ ተገቢ ነው። በማለት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የሸጥኩለት መኪኖች የምርት ጥራት ጉድለት የለባቸውም ።ተጠሪ እስከ ሃያ ሺህ ኪሎ ሜትር ዋስትና ስልሰጠ መኪኖቹ በአገልግሎት ምክንያት የደረሰባቸውን ጉድለት ሁሉ ጠግኘ አሰረክቤለሁ በማለት ተከራክሯል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ክስ የቀረበበትን የመኪኖቹን ቀሪ ዋጋ ከነ ወለዱ ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የመኪናዎቹን ግማሽ ዋጋ በመክፈል መኪኖቹን ተረክቦ እንደ ወሰደና በመኪናዎቹም እየተገለገለ መሆኑ ተረጋግጧል። ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ለመኪናቹ ቀሪ ዋጋ መክፈያ ይሆኑ ዘንድ አምስት ቼኮችን ቆርጦ ከሰጠ በኃላ ክፍያው እንዳይፈፀም ለባንክ የዕግድ ትዕዛዝ እንዳስተላለፈ ግራ ቀኙ ያልተካካዱት ነጥብ ነው። አመልካች አለ የሚለው ጉድለት መጠን ገምቶ እንዲስተካከልለት ወይም ጉድለቱን ለማስተካከል ያወጣውን ገንዘብ ተጠሪ እንዲተካለት ያቀረበው የተከሳሽ ከሰሽነት ክስ ወይም የመቻቻል ጥያቄ የለም።ይህ ከሆነ አመልካች በመኪናዎቹ እየተገለገለ መኪኖቹ የምርት ጥራት ጉድለት አላቸው የሚል ክርክር በማቅረቡ ብቻ የመኪኖቹን ያልተከፈለ ግማሽ ዋጋ ከመክፈል ነፃ የሚሆንበት የሕግ ምክንያት የሌላ መሆኑ ይኸ ሰበር ችሎት አመልካችና ተጠሪ ተመሣሣይ በሆነ የፍሬ ነገርና የሕግ ጭብጥ ላይ በተከራከሩበት በሰበር መዝገብ ቁጥር 95110 አስገዳጅ የሕግ ትርጉምና ሰፊ ትንተኔ ሰጥቶበታል።

በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በቼክ ፅፎ የሰጠውንና ቼኩ እንዳይከፈል ለባንክ የዕግድ ትዕዛዝ በማስተላለፍ ያልከፈለውን ከተጠሪ የገዛቸውን መኪኖች ግማሽ ዋጋ ማለትም ብር 435,554.44 /አራት መቶ ሰላሣ አምስት ሺ አምስት መቶ ሃምሳ አራት ብር ከአርባ አራት ሣንቲም/ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ መሠራታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል።

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል።

2. በዚህ ፍርድ ቤት ሀምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል።ዕግዱ የተነሳ በመሆኑ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ።

3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለያራሳቸው ይቻሉ።

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።**

**ሩ/ለ**